# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ


የመፅሄት አዘጋጅ በርድ፥
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN



ቁጥር፥ 3
ጥር 1966

## የመንግስቱን ጋዜጦች ስናገላብጥ:

### ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ፍርድ:

'ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ' የሚለውን የአጼ ኃይለ ሥላሴን መጽሀፍ አነበብነው:: አጼ ኃይለ ሥላሴ ባለፉት 60 ዓመታት ቢከፋም ቢለማም በኢት ታሪክ ውስጥ ቦታ ያላቸው ሰው ናቸው:: አንዳንዱ በኢት እንደሳቸው ታላቅ ሰው ታይቶ አይታወቅም ይላል:: አንዳንዱ ደግሞ በኢት እንደሳቸው ከሃዲ ታይቶ አይታወቅም ይላል:: ከወደያም ከወደህም ለመለየት የማይደፍረው 'በለጥ' ደግሞ እንደሁ በደፈናው እንደሳቸው ታይቶ አይታወቅም ይላል:: በመሃል ታዲያ አጼ ኃይለ ሥላሴ ራሳቸው 'ህይወቴና የኢት እርምጃ' የሚል መጽሃፍ ይዘው ብቅ አሉ::

አንዱ ሰው: ለዚያውም ደግሞ አጼ ኃይለ ሥላሴን ያህል ሰው የህይወቱን ታሪክ ጻፍኩ ሲል ከሱ የሚጠበቀው ምንድን ነው። መጀመሪያ ነገር መቸስ በህይወቱ የተደረጉትን ዋና ዋና ነገሮች በሙሉ ይተርታል:: ከዚያ ደግሞ በማህበራዊ ኑሮው ውስጥ ለፈጸማቸውና አከራካሪ ለሆኑ ጉዳዮች በበኩሉ ያለውን ማብራሪያና አስተያየቱን ያቀርባል:: እንደያውም ከዚያ አልፎ ተርፎ መሄድም አለበት:: ይህም ማለት አንዳንዱ ገና ሰፊው ህዝብ የማያውቃቸውን ጉዳዮችና ጉደችም አያነሳ በነሱም ላይ በታሪክ የፍርዱ ወንበር ፊት ቃሉን መስጠት አለበት:: እንግዲህ ከኃይለ ሥላሴ መጽሃፍ የጠበቅነው ይህን ይህን ነበር:: ግን ተሠራልን:: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መጽሃፍ ከምኑም የለበት:: በህይወታቸው ያደረግዋቸውን ዋና ዋና ድርጊቶች እንኳን በወጉ አይዘረዝርዋቸውም:: ስለ አጼ ኃይለ ሥላሴ የህይወት ታሪክ ማንም ተራ የፈረንጅ ከበርቴ የጻፈውን መጽሁፍ ያነበበ ሰው

ከባቸው ከሰማው ይበልጥ አበር አጼ ያውቃል፡፡ እቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያን ልብ ብሎ ያነበበ ሰው ይበልጥ መረጃዎች ያገኛል፡፡ ከሸማግሌ ተጠግቶ በቃል ነገር ያወራ ሰው ስለዘመኑ ይበልጥ የተሟላ ዕውቀት ይኖረዋል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ አከራካሪ በሆኑት ጉዳዮች ላይ እንኳን አጥጋቢ ይቅርና ምንም መረጃዎች አይሰጡም፡፡ ከሁሉ የባሰ ደግሞ ዕውነት እንደተቀበረች የምትቀር አርገዋታል መሰል በያለበት የታሸገው አርሸቦ አስቲከፈት ቀናቸውን በሚቀጥሩት ጉዳዮች ላይ ባንቲም አያነሱም፡፡ ነገ፡ መጥው ትውልድ የኃይለ ሥላሴን ዘመን በሚመዘግበት ጊዜ እነዚህ የታሸጉ መረጃዎች መቅረባቸው አይቀርም፡፡ ታዲያ በዚያን ጊዜ የህይወቴን ታሪክ እጽፋለሁ ብለው ከተነሱ ወዲያ የረሱዋቸው መስለው በማለፋቸው ብቻ አጼ ኃይለ ሥላሴ በእነዚህ ድርጊቶች የሚያፍሩ ለመሆናቸው ተጨማሪ መረጃ ተያዘባቸው ማለት ነው፡፡ ለጠላት ይመቻሉ፡፡ ለወዳጅ ያስቸግራሉ፡፡ አለአድልዎ አፈርዳለሁ ለሚል ህሊና ደግሞ ከፉ ጥርጣሬን ያሳድሩበታል፡፡

ስለ አጼ ኃይሉ ሥላሴ የህይወት ታሪክ ለመተረቱ አልተነሳንም፡፡ ስለዚህም በዚች መጽሀፋቸው ውስጥ 'የረሱዋቸውን' ነገሮች ሁሉ እናስታውስ አንልም፡፡ የሚያድበሰብሱዋቸውን ጉዳዮች ሁሉ እናብራራ አንልም፡፡ የሚያጣምሙቸውን ህቆች ሁሉ እናቃና አንልም፡፡ ሌላ መጽሀፍ ይሆንበናል፡፡ ደግሞስ ገና ሳይገነባ የተመረኮዘ ስራ ምርምር ሳይደረግ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ዘመን ማን ሊመዘነው ይቻላል፡፡ ለነገሩ ግን እንጻፍ ብንል ስለዚሁ መጽሀፍ ብቻ ሌላ መጽሀፍ መጻፍ ይቻላል፡፡ መጀመሪያ ነገር አርዕስቱ ራሱ።



"ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" በጣም ጉረኛ አርዕስት ነው፡፡ አንዱ ሰው አንዱን አገር አያራምደውም እንጂ አጼ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን ሺህ ጊዜ ቢያራምዱ እንኳን እንደህ ብሎ አይጻፍም። ነውር ነው፡፡ ሁለተኛ ነገር ደግሞ አጼ ኃይለ ሥላሴን ትተን ስለ 'ኢት እርምጃ' እናውራ ብንል እንኳን በዚህ ዘመን የተገኘው እርምጃ ጥቂቶች የተጠቀሙበት እንጂ አብዛኛው የኢት ህዝብ ከርሀብና ከድቁርና ጋል ተላቀቀበት መሆኑ ግልጽ ስለሆነ 'የኢት እርምጃ' ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም፡፡ ቀጥፈት ነው፡፡

ለነገሩ ግን ለማንሳት የምንፈልገው በአጻጻፉ ዘይ ላይ የታዩትን አይን የሚያወጡ ጉዶች ነው፡፡ እስከ ዛሬ የምንሰማው አጼ እስተዋይ **ብልህ** ቀራጥ ባጭሩ ታላቅና ገናና መሪ ሲባሉ ቸው ነበር፡፡ ግን መጽሀፋቸውን ያነበበ ሰው ፈጽሞ ገራ ይጋባል፡፡ በተለይ ወደ መጨረሻው ላይ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዓይን አፋርነት የሚያጠቃቸው ሰው ይመስላሉ፡፡ በምንም ጊዜ በምንም ቦታ በምንም ጉዳይ ላይ የመሪነት ቦታ ሲወስዱ አይታዩም፡፡ ኢትዮጵያን ያህል አገር እራመዱሁ ብለው መጽሀፍ ለመጻፍ ደፍረው የተነሱ ሰውዩ 'ህዝቡና' 'ተራ ሰዎች' የሚሉዋቸው ኢትዮጵያውያን ሲታገሉ አንዳንዴ በገላጋይነት፡ አልፎ አልፎ በተከታይነት ይገቡ እንደሆነ እንጂ እንኳን ሰመሩ ይቅርና በቀጥ ወገን ሲሉም አይታዩ፡፡

ልጅ እያሱ እንዴት ተገለበጡ። ለምን ተገለበጡ። ሲባል 'በተራ ሰዎች' እየተመከሩ ህገሪቱን ወደ ጥፋት ስለመርዋት 'ህዝቡ ልጅ እያሱን መሻር አስፈላጊ መሆኑን ስለተረዳ ስራ መታ' ይሉናል፡፡ አጼ ኃይለ ሥላሴስ። እባቸው ፈጽሞ በነገሩ የሉበትም፡፡ ህዝቡ አሁንም ስራውን በመቀጠል 'የአጼ ምኒልክን ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱን እንግሠን

የልዑል ራስ መኮንንን ልጅ ደጃዝማች ተፈሪን አልጋ ወራሽና የመንግሥቱ እንደራሴ እናደርጋለን እያሉ ሲራመቱ::’ እንዲህ ነው የሚሉት አጼ ሲተርቱ:: ይህ ሁሉ ሲሆን አባቸው የት ነበሩ:: በእርግጥ የሚታወቅ ነገር የለም:: ዋናው ነገር ብቻ ሲራውን አለመራሁም ነው የሚሉት:: እንደያውም ነገሩ ከተቀረጠ በኋላ ነው ‘በህዝቡ’ ተጠይቀው በጉዳዩ የገቡበት:: ‘እኔንም በምክሩ ውስጥ እንድገባበት ቢጠይቁኝ’ ይላሉ አጼ ሲጽፉ “እኔንም በምክሩ ውስጥ እንድገባበት ቢጠይቁኝ ‘ከእናንተ የምለይበት ነገር የለም’ አለኳቸውና ወደፊት ለህዝቡ ማስረጃ እንዲሆን የጻፉትን ሁሉ እያነበቡ አስረዱኝ::” ባጭሩ አጼ ኃይለ ሥላሴ ህዝቡን መርተው ሳይሆን በህዝቡ ተመርተው አልጋ ወራሽ ተባሉ:: ግን ታዲያ ልብ ላለ ሰው ገራ የሚያጋባ ነገር አለ:: ህዝቡ ገና የሲራውን ነገር ሳያነሳ ‘ልጅ እያሱ በተንኮል አልጋቸውን ሳለፈለገ ጳጳሱ ጋር ወስደውኝ አስምለውኝ ነበር’ ይላሉ:: ለነገሩ እንኳ ልጅ እያሱ የተባሉ ሰው ከዚያ ሁሉ መኳንንት መርጠው ራስ ተፈሪን ጉትተው ‘ና ማልልኝ’ ማለታቸው እንዲሁ በባዶ ሜዳ ከፉ ጠርጣራ ሰው ነበሩ ማለት ነው::

በዚህ በኩል መቸስ ከሁሉ የሚያስቀው:/የሚያስቀው እንበለው እነጂ እንዲህ ያለ ገራ የገባው ነገር/ አጼ ሳያሰሙት ንገሡ የተባለው ዱብ ዕዳ የወደቀባቸው ጊዜ አባየሁ የሚሉት መጨነቅና መገደርደር ነው:: እዚህ ላይማ ጭራሽ ህዝቡ በድንገት ተቀጥቶና አድማ መትቶ ንገሡ እያለ ሲያስጨንቃቸው ‘የለም ቀስ ብዬ አደርሳለሁ’ እያሉ ሲጋበዙ ነው የሚታዩት:: በዚያን ዘመን አጼ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ፊውዳሊስቶች አንድ ክንፍ ይመሩ እንደነበረና በዚህ ትግል



ደግሞ ከንግሥት ዘውዲቱ ጋር እየደጋገሙ ይጋጩ እንደነበረ ማንም የሚያውቀው ነገር ነው:: የንጉሥነቱንም ማእረግ ያገኙት ተገደው ሳይሆን አስገድደው ሲራ መትተው ከንግሥት ዘውዲቱ ወገኖች በተለይ ከነደጃዝማች አባ ውቃው ጋር ፊቱ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በመሣሪያ ተፋጠው እንደ ሆነ ማንም የሚያውቀው ነው:: ሌላው ቀርቶ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ የጻፉትን መጽሃፍ ያነበበ ሰው ይህን የሥልጣን ሽሚያ በደንብ ሊረዳው ይችላል:: አጼ ኃይለ ሥላሴ ግን ንጉሥነቱን ‘ቢጨንቀኝ አሸ አልኩ’ ነው የሚሉት:: የሳቸው አገላለጽ እንደዚህ ነው፦

“ከተሰበሰቡት መሀከል ሶስት ሰዎች ጠርቶ የመንግሥቱ ሥራ ሳይከፋፈል በአንድ ሰው ብቻ እንዲሠራ ያሳሰባቸሁት ሀሳብ ጥሩ ነው:: እንጂ የንጉሥነቱ ነገር ባይነሳ ጥሩ ነው::... ...ይህ ነገር እንዲቀር አድርጉ ብዬ ወደ ህዝቡ ዘንድ ብልካቸው ‘እኛ ለማንም ሳናዳላ ለመንግሥታችን ክብር ለህዝቡ ጥቅምና ሰላም እንዲሆን አስበን የተነሳንበት ነውና ወደ ኋላ ለመመለስ አንችልም’ የሚል ቃል ሰለ ላኩብን ዝም አልን::”

ማለት ደጃዝማች ተፈሪ ሳያስቡት ዝም ብለው ንጉሥ ሆኑ:: እንደ ዩል ዩስ ቄሳር ታሪክ ‘ዘውዱን ሶስት ጊዜ ሲጥሉልኝ ሶስት ጊዜ መለስኩት’ አለማለታቸውም ተመስገን ነው:: በነገራችን ላይ ታዲያ አጼ ኃይለ ሥላሴ አምና ለአንደት የጣልያን ሴት ጋዜጠኛ በሰጡት ኢንተርቪው ላይ ‘ንጉሥ መሆን ደስ ይለዉታል ወይ’ ተብለው ሲጠየቁ ‘አወን ህይወታችንን ሁሉ የኖርነው ለዚሁ ነው’ ብለው ነበር:: ታዲያ እንዲህ ተሆነ አልነግሥም እያሉ ‘ሲያስቸግሩ’ ህዝቡ ባያግደረደራቸው ኖሮ ምን ሊውጣቸው ኖሮ ዋል።

ግን እኮ ይህ ሁሉ ቀልድ ነው:: እንዴ! ‘በዚህ ዓላማ ተመርቸ በማምንበት ጉዳና ህዝቡን መርቸ እንዲህ አርጌ ሰልጣን ጨበጥሁ በዚህ ዓላማ ተነስተው ከህዝቡ ጥቅም ጋር በዚህ በዚህ

ነጥበ ላይ የሚጋጭ ሃሳብ ይዘው እነአገሌ እነአገሌ ቢነሱ ታላቅ ተጋድሎ አድርጌ ጣልካቸው::» እየተባለ ቢጻፍ አከ ሙንም ነውር የለውም:: አንድ ሰው መቸስ ታላቅ ሰው የሚባለው ለዓላማው በግንባር ቀደምነት እየተነሳ ተከታዮቹ ሲያፈሩና በቆራጥነት ሲታገል ነው እንጂ አጼ ኃይለ ሥላሴ እንደሚሉት እንዴት እርምጃ በወሰደ ቁጥር እየተግደረደረ 'ግድ የለም ቀስ በየ አደርጋለሁ' እያለ መሪነቱን ትቶ በተከታዮቹ ሲገፋና ሲነዳ አከ አይደለም::

አጼ ኃይለ ሥላሴ ነገር ያሳመሩ መስለዋቸውም እንደሆን እንጂ በመራራ ትግልና በመሪነታቸው ያገኙትን ድል ሁሉ ተለምነው የተጎናጸፉት ያስመስሉታል:: ለአመኑበት ዓላማ በግንባር ቀደመነት መታገልን መውጣት መውረድን ነውር አርገውታል መሰል ዘፋኔን ከእግዚአብሄር ታድዩ ነው እንጅ ከሰው ታግዩ አገኘሁት አይሉም:: ባጭሩ አጼ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን 'ሲያራምዷ' እሳቸው እራሳቸው መራመድን እረስተውታል መሰል የመረጡት የታሪክ አጻጻፍ ዘዴ ያው የጥንቱ ከማቀባባ ያረጀው የታሪክ አጻጻፍ ዘዴ ነው:: ይህንንም የታሪክ አጻጻፍ ዘዴ የዛሬ 60 ዓመት አስተዋዩ ምሁር ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ 'አጼ ምንሊክና ኢት.' በሚለው መጽሀፉ ውስጥ ግሩም አድርጉ አቀርበታል:-

«አንድ ንጉሥ እንደህ አርጉ ጥሮ ነገሠ: ከነገሠም በኋላ በእንደዚህ ያለ ምክንያት ይህንን ፈጸመ:: ይህንንም ተወ:: በእንደዚህ ያለም ነገር ወደቀ ወይም ለማ ከሚሉዋቸው ይልቅ እገሌ ከሰማይ ወይም ከጠንቋይ እንደህ ያለ ትንቢት መጥቶለት ለመንግሥት የተወለደ ሰው መሆኑን አውቆ ታውቆ እገሌና እጌሌ ታጠቁለት: እገሌና እገሌም ሰይጣን አስተዋቸው ተዋግተውት አሸነፋቸው:: ነገሠም:: ከነገሠም በኋላ እገሌ ናዝሬዊ መከርት ይህንን አደረገ:: ከሠይጣን ቢፋቁር እንደህ ዓይነት ጉዳት ወረደበት:: በፍካሬ እየሱስ የተነባው ጊዜያቱ ተፈጸሞ ሞተ



ብለው ቢጥሉዋቸው ይወደሉ:: ጉልበት የሌለው ብዙ ንጉሥ ኖርዋል ይኖራልም:: ነገር ግን የታሪካችን ቃል ዐውነት ከሆነ ዘንድ እንደዚሁ በብዙ የቀደሳንና የአጋንንት ርዳታ እንደኢትዮጵያችን ነገሥታትና ገዥዎች የሚያስፈልገው ሰው በዓለም ታሪክ ከቶ አልተሰማም::»

የአጼ ኃይለ ሥላሴን ታሪክ አጻጻፍ በቀጥታ በዚህ ዓይነት ዘዴ የሚጠቀም ለመሆኑ አንባቢ ያስተውለው ከማለት በቀር እና እዚህ ላይ የምንጨምረው የለንም:: እንደዚህም ስለሆነ ይህ መጽሃፍ ለአንባቢ የሚሰጠው ቅንጣት ትምሀርት የለውም:: ድል ባደረጉ ቁጥር የትግሉን ዘዴ ማተት ትተው 'በእግዚአብሄር ኃይል አሸነፍን' ይሉናል:: ድል በተነሱ ቁጥር ደግሞ 'እግዚአብሄር ከኛ ጋር አልዋለም ብለው ይዘጋሉ::' ከዚህ ይልቅ የጠላቶቻቸውን ኃይል የወገኖቻቸውን ደካማነት የተደረጉትን ስህተቶች ቁልጭ አድርገው ቢያሳዩን ይሻለን ነበር:: 'ካ' ባለቻ ቁጥር በኔ በኩል ተሰለፈ የሚሉትን ሁሉ እንደዘሁ 'ህዝቡ' እያሉ በደፈናው ቢያትቱልን ምርመራችን ሊራመድ አይችልም:: ጠላቶቻቸውን ሁሉ ደግሞ 'ተርታ ሰዎች ክፉ ሰዎች' እያሉ በቀላሉ ሊያስናብትዋቸው በሞከሩ ዓላማቸው ያልተብራራለት አንባቢ 'ተርታ ማለት ምን ማለት ነው ክፋታቸውስ የት ላይ ነው' ብሎ መጠየቁ አይቀርም::

የሆነ ሆኖ አጼ የህይወት ታሪካቸውን ጻፉ ሲባል ከሁሉ የጓጓነው ከጣልያን እምፔር ያሊዝም ጋር ስለተደረገው ትግል አንዳንድ ማብራሪያዎች ይሰጡናል ብለን ነበር:: የጣልያን እምፔር ያሊዝም ወደ ኢት. መምጣት በሃገሪቱ ገዥ መደብ ውስጥ ብዙ ውዥንብር ውዝግብና መካካድ ማስከተሉ የታወቀ ነገር ነው:: አጼ ኃይለ ሥላሴ እዚህ ሁሉ ውስጥ ዓይነተኛ ቦታ ነበራቸው:: በኢት. ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጦር ሜዳ ተመልሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የጠላት ጦር አገሪቱን ይዞ አንድ ንጉሠ ነገሥት

አገር ጥሎ ሄደ:: ለጥቂት ጊዜ የተደናገጠው ህዝብ መልሶ
ነፍስ እንደዘራበት ኃይለ ሥላሴን እንደረሱት አረስቶ የገዛ
መሪዎቹን እየመረጠ የአርበኝነት ትግሉን ጀመረ:: በመሃል
አጼ ኃይለ ሥላሴ አገር ለቀው በሄዱ በአምስት ዓመታቸው ኢምፔ
ር ያሊስት ጣልያንን ለማስወጣት አካባቢውን ከያዘው ኢምፔሪያሊ
ስት ከእንግሊዝ ጋር 'ቃል ኪዳን ተጋባሁ' ብለው ጦር እየተከተሉ
ተመለሱ:: ለሃገራቸው ነጻነት በዱር በገደሉ የተሰማሩት አር
በኞች 'የሸሸ ንጉሠ አይገዛንም። ነጩን አህያ አባረን ሙላ አህያ
እንግሊዝ አይገዛንም' እያሉ አንገራገሩ:: እነዚህ አገር ወዳዶች
በአጼ ኃይለ ሥላሴና በእንግሊዞች እየታደኑ ተገደሉ:: እንግሊዝ
ኢትዮጵያን በፕሮክቶሬት መልክ መያዝ ጀምራ ለመደላደል ስትታገል
የባሰ ኃይለኛ አጋጥሞዋት አስር ዓመት እንኳን በወጉ 'ሳትበላ'
በታዋን ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ለቀቀች:: ዛሬ አሜሪካን
ዜፋ ኔን ጠብቀልኝ እንጂ፣ ከዘረፋው አጉርሰኝ እንጂ፣ ከህዝቡ
ጠብቀኝ እንጂ ኢትዮጵያን እንደፈለግህ ተብሎ ሃገሪቱን እያን
ሠራራ በመያዝ ላይ ይገኛል:: ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን አጼ
ባለፈው መጽሃፋቸው ውስጥ ያላብራሩልን/በዚህ አያያዝ ደግሞ
ወደፊት ይመጣሉ የተባሉት ሰባት ጥራዞች 'ረስተዋቸው' የሚያ
ልፍዋቸው/ መዓት ጉዳዮች ሲኖሩ ነው::

ደስ የሚለን በነዚህ ጉዳዮች ላይ አጼ አንዳንድ ነገሮ
ችን ቢያብራሩልን ነበር:: ለምኑ ነው? ዛሬ እንደሆነ በያለበት
አርሸሽ እየተከፈተ ሄዱዋል:: ጉዱ ሁሉ በመጋለጥ ላይ ነው፤
ለሳቸውም ለራሳቸው ቢሆን እነዚህ ጉዶች ምንጊዜም አይታወቁኝ
ብለው ዝም ከማለት እያነሱ በነሱ ላይ ቃላቸውን ቢሰጡ ይሻላ
ቸው ነበር:: አረሳሁዋቸው ሊሉ አይችሉ ምክንያቱም እነሱን
ከረሱ የህይወት ታሪክን መጻፍ 'ምን ይዞ ጉዞ' ይሆናል::

በበኩላችን የጣልያን ጊዜውን ታሪክ ለመጻፍ አልተነሳንም



ግን አንዳንድ የተረሱ ጉዳዮችን ለማንሳት እንወዳለን::

መጀመሪያ ነገር ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊትና ከዚያም
በኋላ አጼ ኃይለ ሥላሴ በምስጢር ከሙሶሎኒ ጋር ይላላኩ
እንደነበረ ዛሬ አንዳንድ መረጃዎች ተገኝተዋል:: በተለይም
በኤርትራና በሱማሊያ የጠላት ጦር እየተከማቸ ሲሄድና ጣልያ
ን በያለበት ብዙ 'መኳንንት' እንዳስከዳ ሲያረጋግጡ፣ የሚወ
ዷት ዘውዳቸው ከጭንቅላታቸው ላይ ስትበር የተሰማቸው አጼ
ኃይለ ሥላሴ ራሳቸው ከጣልያን ለመታረቅ ፈልገው እንደነበረ
አሁን የታወቀ ነገር ሆኗል:: ለዚህም አንዳንድ መረጃዎች
ከመገኘታቸው በላይ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በሙሶሎኒ መካከል
በተላላኪነት ሽር ጉድ ይሉ የነበሩት ግለሰቦች ታሪካቸውን
ጽፈዋል:: ከነዚህም መካከል ለምሳሌ ሙሴ ዱሩፍ የተባሉ ፈረ
ንሳዊ፣ ፍሉጥ የ ሲቪቺ /የጊዜው የጣልያን መንግሥት የጭፍ ጉ
ዳይ ሚኒስተር/ ፍራንሲስ ሪኬት/ የቀድሞ የኢት. ባንክ ገዥ
ተውፊክ ደስ ፖሻ፣ ሹክሪ ያሽር ወዘተ. የተባሉ ሰዎች ይገ
ኙባቸዋል:: በዚያን ጊዜ አጼ ኃይለ ሥላሴ ለሙሶሎኒ የሚያ
ቀርቡት ሃሳብ ምን ነበር:: እሳቸው የሚሉት 'ዘውዴን ለኔና
ለወገኖቼ /ለዘሬ/ ተውልኝና ኢት. በጣልያን ስር ፕሮቴክቶሬ
ት ሆና እኔ በእንደራሴነት ላስተዳድር' የሚል ነበር:: መጀ
መሪያ ሙሶሎኒ ይህን ሃሳብ ወደ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር ሰው
መላክ ጀምሮ ነበር:: በኋላ ግን የኢትዮጵያን ገዥዎች ቦርቡ
ሮና ከፋፍሎ ስለነበረ፣ የጣልያኑ ዋና የጦር አዛዥ እንዳለው
ጦርነቱ ሳይጀመር ከኢት. ጦር 200 መቶ ሺህ ሰው የሚያዙ
መኳንንት ስላስከዳ፣ በተለይ ደግሞ በሱዳን በኩል ጣልያ ገብ
ታ ታስቸግረኛለች ብሉ የሚፈሩት እንግሊዝ ዝም እንድትል
ስለተረዳ፣ ብዙ ካመነታ በኋላ ይህን ሀሳብ ሳይቀበለው ቀረ::
በሚቀጥለው መጽሀፋቸው ውስጥ ካልተረሳ በስተቀር ተመልሰው
አዲስ አበባ የገቡ ለት ባደረጉት ዲስኩር ለሙሶሎኒ ልግባ
ብለው ያቀረቡት ይህ የፕሮቴክቶሬት ሀሳብ ተቀባይነት ባለማግ
ኘቱ በሙሶሊኒ ሲያማርሩ አጼ ኃይለ ሥላሴ እንዲህ ብለዋል::

«ምንም ለአንድ ነጻ መንግሥት ከባድ ቀንበር ሆኖ የሚቆጠር ቢሆን የማንጻ ወይም የኘሮተከተሬት አስተዳደር አንዷን አላሰበላትም::»

አያን ሙሶሊኒ ትርፍ ፈለጉ እምቢ አለ::ግን ይህን ዓይነት ቀኝ አገዛዝ እምቢ ያለው እሱ ብቻ አልነበረም:: የኢትዮጵያ አርበኞችም ይህን ከባድ ቀንበር እምቢ በለው በዱር በገደሉ ጠላታቸውን ተቋቋሙ::በመሃል ነገሩን ሁሉ ትተው ከነፍሳቸው የሚወደትን ዘውዳቸውን ተሸክመው ባህር የገቡት አጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሆኑ::

ግን ባህር ከመግባታቸው በፊት ሌላም ያልተነገረን ብዙ ቁም ነገር አለ::ሙሶሊኒ እምቢ ሲል ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተሳሳከው ይህንኑ 'ዘውዷን አትንኩ አገር ይኸው ላቸሁ' የሚለውን ሃሳባቸውን አቀርበው እንደነበረ የሚመሰክሩ የምስጢር መረጃዎች ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መውጣት ጀምረዋል::ይህን መልእክት ደግሞ ለእንግሊዝ የላኩት ወደ ማይጨው ሲዘምቱ ደሴ ላይ ሆነው ነው::እዚህ ላንጠቀሻቸው በማንችላቸው መዓት ምክንያቶች የተነሳ ለግዜው እንግሊዝም ይህን የኘሮተከተሬት ሃሳብ እምቢ አለች::ለግዜው አልን:: በኋላማ እሽ ብላ ኃይለ ስላሴን በል ምራ እያለች አገር ለትይዝ ተመጣለች::/

አጼ ባያበራሩ ያለፉት ለአደሉ ትውልድ ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉበት ሌላ መዓት ነገር ነበር:: ለምን በቀላሉ..ተሸነፍን:: አጼ ገና ማይጨው ሳይደርሱ 'ምናልባት ጠራቸን ዱላ የሆነ እንደሆነ' በለው 'የምንልከው ቃሉ አምላካችን ካኛ ጋር አልወጣም' የሚል እንደሆነ አስታውቀዋል:: ከመጀመሪያውም ለማንኛውም ብለው 'በጠሬ አልታመንም ዱላ የእግዚአብሄር ነው' በለው ጨርሰዋል:: ግን እኮ ታደያ እግዚአብሄርን ተማምነው ያወጡት የጦር ኃይላን የተከተሉት ፖለቲካ መዓት ምህረት የማይደረግለት ስህተት ነበረበት::



ለምን ተሳሳቱ አንልም:: ሰው ናቸው:: ለምን በእግዚአብሄር ተማመኑ አንልም:: ሃይማኖት የግል ነው:: የተደረጉትን የፖለቲካና የጦር ስህተቶች በእግዚአብሄር አይለጥፉ ነው የምንለው::

ዛሬ እንዳንዱ ዘመቻ በተለይ ደግሞ የተንቤንና የአምባራዳም ጦር ከተፈታ በኋላ ማይጨው ላይ የተደረገው የፊት ለፊት ጦርነት የአጼ ኃይለ ሥላሴና የገዥወቻቸን ክብር የሚጠይቀው ወንጀል እንጂ በዚያን ጊዜ በዚያን ቦታ በዚያ አመራር ጣልያንን ፊት ለፊት መግጠም የጦር ታክቲክ 'ሀሁ' የሚከለክለው፤ብዙ የኢትዮጵያ ወጣቶችና አርበኞች የተቃወሙት፤ የውጭ አገርም አማካሪወች ህዝቡን እንደ እሳት ራት ማድረግ ነው ያሉበት ትልቅ ስህተት ነበር:: ከማይጨው በፊትም ሆነ ከማይጨው በኋላ/በተለይ የራስ እምሩ ጦር በሰተሰሜን ዘምቶ በደፈጣ ጦርነት ያገኘው ምያና በጠላት ጦር ላይ ያደረሰው ጉዳት ሲታይ፤ እንደሁም ዳግሞከማይጨው ጦርነት በኋላ የአምስት አመቱ የአርበኝነት ታሪክ ሲመረመር/ እንደህ ታጥቆ የመጣን ጦር ማዳከምና መሰበር የሚቻለው በደፈጣ ጦርነት ነበር:: ግን ይህ ደግሞ 'የሸፍታ ጦርነት' ነው:: እነ ኃይለሥላሴ ደግሞ ባይሆን 'ማንዴት ወይም ኘሮተክተሬት' እያሉ 'ከባድ ቀንበር' ይቀበሉ እንደሆን እንጂ፤ ወይም ደግሞ እንዱን ህዝብ እንዳለ ነዱተው ያጋፍጡ እንደሆን እንጂ እነደ አንድ ተራ ሸፍታ ለማዱፈጥ ክብራቸው አይፈቅዱላቸውም:: ብቻ ይህንን ለዕውነተኛው ታሪክ ጸሀፊ እንተወውና ሌሎች የተዳበሰበሱ ጉዳዮችን እናስታውስ::

በዚሁ በጣልያን ግዜው ጉዳይ:: አገር ጥለው ለምን ሄዱ::ህዝብ ተጋፍጦ መታረዱን እናውቃለን። ያውቃሉ:: የኢት. ህዝብ በረጅም እኩሪ ታሪኩ እንደዚያች ሰዓት መሪና ሰበሳቢ አስፈለጉት የሚያውቅ አይመስለንም:: በእንደዚህ ዓይነቱ ወቅት በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አንድ ንጉሠ ነገሥት ከጦር

ሚዳ ተመሰስ ከዚያም አልፎ ተርፎ ከነጭራሹ አገር ለቆ ሲሄዱ ቢያንስ አከራካሪ ሲበዛ ደግሞ ከታሪክ ከሀደት የሚቆጠር ድርጊት ነው:: እዚህም ላይ ታዴያ በተበራሪ አነጋገጀ በታሪክ የፍርዱ ወንበር ፊት ቃላቸውን ቢሰጡ ለናም ለባቸውም ይሻላቸው ነበር:: በዚህም ላይ እነአዲስ ዘመን ከሚነዙት በሬ ወለደ አንካን ጠለቅ ያለ መረጃ አይሰጡንም:: መጀመሪያ ጦሩ ማይጨው ላይ ሲፈታ ‘እዚቸው እመታትለሁ ብለው ቢያስቸግሩ መኳንንቱ መክረው ተቆጥተው: ጸጸባቱ ገዝተው ከሞት አፋፍ’ የተመለሱ መሆናቸውን ከአበሳ ባዩ ታሪክ አንብበን ነበር:: ይህንን እጼ እምብዛም አያነሱት:: ዋናው ነገር ግን ከማይጨው መልስ የሆነው ሰንቅ በሚገኝበት አገር እየተዘዋወርን በረዥም ጊዜ ጦርነት እናሸንቸግረው በሚል ሀሳብ ተቆርጦ ነበር:: እጼም ባስነገሩት አዋጅ ላይ ‘ስንቅ በሚገኝበት አገር ታላቅን ጦርነት ለማድረግ ወደ ሸዋ ተጉዘናል’ ይሉ ነበር:: ነገር ግን አዲስ አበባ የደረሱ የእለቱ ለት እጼ ያሰወጁትን ‘ታላቅ ጦርነት’ እርግፍ አድርገው ረስተው በድንገት የጅቡቲ ደንሎማት ሆኑ ተገኙ:: በዚህም የተነሳ ‘ቆርተው ይዋጉ አለበለዚያ የተሸበረው ህዝብ የባሰውን ተስፋ ይቆርጣል’ ከሚሉት ከነታከለ ወልደ ሃዋርያት: ከነ ፍቅረ ማርያም አባ ተጫንና ከተቀሩት የኢት. አርበኞች ጋር የመረረ ጠብና ክርክር ተነሳ:: እጼ መጽሃፍ ውስጥ የዚህ ክርክር ዝርም የለ:: ዓይን በሚያወጣ አኳኋን ነገሩን ሁሉ በማጣመምና በማጭበርበር የነበረውን ምርጫ ሲያቀርቡት ፈጽሞ መፈናፈኛ የሌለው ጉዳይ ያደርጉታል:: የነበረውን ምርጫ ሲያስረዱ እንደሁ ይላሉ::

«እንደኛው መዋጋትን ትቶ በምክር እንደተቋረጠው ለዓለም መንግሥታት ለማስታወቅ ወደ ጀኔቭ መሄድ:: ሁለተኛውም በከተማው የተገኙትን ጥቂት ወታደሮች ይዞን የሸማግሌውን የሴቶችና የህጻኑን ሞት የከተማውን መቃጠል ብናስበ መዋጋት ነው:: »

በጭሩ እጼ ኃይለ ሥላሴ ከጅቡቲና ከኩነኔ ምረጥ



ተባሉ ነው የሚሉን:: ይህ ፈጽሞ ውሸት ነው:: ይሄዱ ወይም አይሄዱ በሚሉት መካከል ‘ቆርተው ይዋጉ’ የሚሉትን አርበኞች ወገን ለማጥላላት: ስም ለማጥፋት ፋና ቲኮች ለማስኘት: እጼም አገር ለቆው ሲሄዱ ዐውነታቸውን ነበር ለማስኘት የተደረገ ከንቱ ሙከራ ነው:: እጼ ኃይለ ሥላሴን ‘እይ ግዑ የለም አዲስ አበባ ትቃጠል! የሽማግሌውን የሴቶችና የህጻናቱን ሞት የከተማውን መቃጠል ባይበሉ ተዋጉ’ ያላቸው ማንም አልነበረም:: እጼ ኃይለ ሥላሴን ቆርተው እንዲዋጉ የጠየቀት የኢት. አርበኞች እንደሁ ዓይነት የአሳት ራት ታክቲክ ይዘው አልቀረቡም:: እንደያውም ካለንበ እነታከለ እጼ ኃይለ ሥላሴ ህዝቡን ነድተው እንደ እሳት ራት ማይጨው ላይ ሲወረውሩት ከመጀመሪያው የተቃወሙ: የዘመኑ የጦር ታክቲክ አሳምሮ የገባቸው: በኋላም አውርተው ሳይቀሩ ሙያቸውን በተግባር ያስመሰከሩ ጀግኖች ናቸው:: እተ ሄደም ያልዋቸው ‘አዲስ አበባ ትቃጠል’ ለማለት ሳይሆን: ከአዲስ አበባ ወጥተው: መናገሻ ከተማው ወደ ጎሬ ተዛውሮ በመላ ኢት. እየተዘዋወሩ የአርበኝነቱን ትግል እንደሰበሰቡ እንዲመሩ ነበር:: ምርጫው በከተማው መቃጠልና በእጼ ኃይለ ሥላሴ ጀኔቭ ሄደው ማስታወቅ መሃከል አልነበረም:: የነበረው ምርጫ በመሸሽና ቆሞ በመዋጋት፣ ሃገርን በመክዳትና ለወገን በመሰዋት መሃከል ነበር:: ለዚህም ማመሣከሪያ ሩቅ መሄዱ አያስፈልግም:: ‘ጀኔቭ ሄጄ ላስታውቅ’ ያሉትና የሃገሪቱን ሃብት ‘ለስንቅ’ ይዘው የወጡት እጼ ኃይለ ሥላሴ ጀኔቭ አልሰማ ሲላቸው ኢትዮጵያዊ ተግባራቸውን ለመፈጸም በዴር በገደሉ አልተሰማሩም:: ‘አዲስ አበባ ትቃጠል’ ብለዋል የተባሉትም የኢት. አርበኞች ጣልያንን ስቃያቸውን እያዩ በዴር በገደሉ ተቋቋሙት እንጂ ከተማ ቁጭ ብለው አልጠበቁትም:: እንዲያው ለነገሩ እናንሳው ማለታችን ነው እንጂ ሽሽቱንም ሆነ አርበኝነቱን አስተዋዩ የኢት. ህዝብ

አሳምሮ ያውቀዋል::
የሆነ ሆኖ አጼ የመረጡትን መረጡ:: ምርጫው የራሳ
ቸው ነው:: ሰው በግድ አገርህን ውደድ አይባልም:: እንኳን
ከምክሩ ውስጥ ያልነበረው ተራው ኢትዮጵያዊ ይቅርና ከርክሩ
ውስጥ የነበሩት አርበኞች አጼ በለሊት ባሩር ሸለከው አደስ
አበባን መልቀቃቸውን ጥዋት እንደመርደ ነው የሰሙት:: ታከለ
አሳምን ብለው አቃቂ ዱረስ ወረደ:: አቀጩን ሲያውቅ 'ወይ
አገሬ በመከራሽ ጊዜ የሚደርስልሽ አጣሽ!' ብለው ሃፍረትና
ንዴት የገፋፋው እንባ እያፈሰሱ ከመሬት ወደቁ ይባላል::
በምክሩና በክርክሩ ጊዜ የደኙን ነገር አጥብቀ ይቃወም የነ
በረውና "ንጉሠ ነገሥታችን አገር ለቀቁ እሸሻለሁ ብሉ በታሪ
ካችን ያልታየ አሳፋሪ ድርጊት አፈጽማለሁ ብሉ እምቢ ካለ
ክብራችን የሚጠይቀውን እርምጃ እንወስዱበታለን" እያለ ሲዝት
የነበረው ፍቅረ ማርያም አባ ተጬንና ሌሎችም መስት አርበኞችም
ኢትዮጵያዊ ተግባራቸውን እየፈጸሙ ለመምት አደስ አበባን
እየለቀቀ በየደኑ ተሰማሩ::

አጼን አገር ለቀው ከወጡ በኋላ ብዙም አንከተላቸው::
ከጣሊያን ተስማምተው 'ዞፋ ነን' ይቁሟል ብለው አንጠልጥለው
የወሰዱዋቸው ራስ ኃይሉ ዱሬዳዋ ላይ አምልጠዋቸው ወደ አደስ
አበባ ተመለሱ:: አጼ ግን ይቸንም ከቁም ነገር ቆጥረዋት
'ፈተን ለቀቅ ነው' ብለው ይጽፋሉ:: ይህ እንኳን 'ሌባ
ከሌባ ቢጣላ በሰው ገለባ' ነውና እኛን አያገባንም:: 'ከዚያ
በእርግጥ የሚታወቅ ነገር ቢኖር ያቸ መከረኛ 'እግዚአብሄርና
ታሪክ.....' የምትለዋ ሉሬንስ ታዐዘዝ የጻፈላቸው ደስኩር
ነቸ:: የአጼ መጽሃፍ ከዚህ አልፍ አይሄድም።እኛም እዚህ
ላይ እንቆማለን::

ከፍ ብለን የጠቀስነው መጽሀፍ ውስጥ አስተዋጹ ነጋዴ
ራስ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ ስለዚሁ ስለ ነገሥታት ህይወት
ታሪክ አጻጻፍ እንስቶ ሲያማርር የዛሬ ሰልባ ዓመት እንደህ



ብሎ ጽፍ ነበር:: 'ነገሥታት በህይወታቸው ባሉ ታሪካቸውን
ያለ ፍርሃት የሚጨወትበት ያርነት ዘመን ሳበሻችን ገና አሎ
መጣም' የነ አደስ ዘመንና የአበሳ ባዩ ታሪክ ጸሀፊ መቀባበ
ት እጅ እጅ ያለን ኢትዮጵያውያን ባዕዳን አርሸሹም እየተከ
ፈተላቸው ሆነ እነ አጼ የሰባቸውን እያጫወትዋቸው /ከኛ እነሱ
ታም ነውሳቸው/ በሟሞጫጭርዋቸው 'የታሪክ መጽሀፍት' ሰንተከዘ
ብዙ ዘመን አልፍን ነበር:: ታደያ አጼ የህይወት ታሪካቸውን
ጻፉ ሲባል ከእውነቱ ትንሸ ሊነገረን ነው የሚል ከንቱ ተስፋ
አድርበን ነበር:: ግን እንኳን ከምናውቀው ሊጨምሩበት ይቅርና
ይቸውም በዛቸ ተበላ ሊያዱበሰብሱን ሞከሩ:: ይህ ራሱ እንግ
ዲህ ከገብረ ህይወት ባይከዳኝ ዘመን እስካሁን ዱረስ ኢት
ሳደረገቸው 'እርምጃ' በቂ ማስረጃ ሊሆን ይቸላል::

ግን ዕውነት እነደተቀበረቸ አትቀርም፤፤ ለኢትዮጵያቸ
ንም የነጻነት ዘመን በርግጥ ይመጣል:: በዚያን ጊዜ ታደያ
በዚቸ መጽሀፋቸው አጼ ኃይለ ሥላሴ በየገጹና በየመሥመሩ የተ
መጻደቁትና የሚያጣምሙት ሀቅ ሁሉ አንዱ በአንዱ ከማትሞተው
ዕውነት ጋር እየተመሳከረ ይጋለጣል:: እሳቸውም ይጋለጣሉ::

በዚያን ጊዜ እነአደስ ዘመን እንደህ አይነቱን ፍሬ
ከርስኪ መጽሀፍ ዓይናቸውን ባያሹ 'ግሩም ድንቅ' ብለው መቀ
በላቸው ብቻውን የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ምን ያህል
የግብዝነትና የከንቱ ውዳሴ ዘመን እንደነበረ ለማስረዳት በም
ስክርነት ይቀርባል:: እንደዚሁም ደግሞ አጼ ኃይለ ሥላሴ
ኢትዮጵያን 'እራመዱሁ' እያሉ በሚደነፉበት ወቅት በመቶ ሺህ
እየተቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በወሎና በትግሬ በርሀብ ሰለሚረ
ገፉ ይህ የሀይለ ሥላሴ 'እርምጃ' ለንጉሠ ነገሥቱና ለገብረ
አበሮቹ መቀናጣት ሲባል የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅ ፍርጃ
ላይ የጣለ መቅሰፍት እንደነበረ በግልጽ ይታወቃል:: ነጻው

ትውልዱም እንደዚህ ዕውነትን ከተረዳ በኋላ አጼ ኃይለ ሥላሴ የመጽሀፋቸውን ስም "ህይወቴና የኢትዮጵያ ፍርጃ" ቢሉት ይሻል ነበር ብሎ ይበይናል:: ይህንንም የመከራ ዘመን በተደራጀ ረዥም ትግል የሚወጣው ነጻ ትውልዱ <u>የኢትዮጵያን ህዝብ የእርምጃ ታሪክ</u> በላቡና በወዙ ለመጻፍ በኩራት አዲስ ምዕራፍ ይከፍታል::

———//———//———

## <u>ከመጽሄት ቦርድ ማሳሰቢያ</u>

### <u>"ት ግ ላ ች ን ዜ ና"</u>

በአውሮጳ የኢት. ተማሪዎች ማህበር የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ በየጊዜው እየታተመ የሚወጣ የዜና የአስተያየቶች መስጫ ጋዜጣ የመጀመሪያውን ቁጥር በጥር ወር ያሰራጫል::

የማህበራት ሃላፊዎችም ሆኑ ግለሰቦች የማህበር ዜናዎችንና ሃሳቦችን ለመጽሄት ቦርድ በየጊዜው እንዲልኩ ያሳስባል:

# ይዘት


1. ርዕሰ አንቀጽ ገጽ 1
2. ረሃብ በኢትዮጵያ 5
3. የዓለም ጋዜጦች የኢትዮጵያን መንግሥት ያወግዛሉ 13
4. የሰብአዊ መብት ዱምፀ 15
5. ለዲሞክራሲና ለፍትህ ለሚታገሉ የተደረገ ጥሪ 18
6. የጊኒ ቢሳዎ ህዝባዊ ትግል 20
7. የመንግሥትን ጋዜጦች ስናገላብጥ 31
   ‘ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ፍርጃ’
8. የትግላችን ትርጉም ‘የመቀሃዱ ዘመቻ’ 46
9. ይድረስ ለትግላችን 56
10. ኢትዮጵያ በዓለም ጋዜጦች 58
    ‘የኢትዮጵያ መንግሥት ለፖርቱጋል ይሰልላል’

ግጥ፡ ‘መንገደኛ’ 62